https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 31
ADDIS ABABA, 24th March, 2017

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻/፪ሺ፱ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……ገጽ ፱ሺ፭፻፺፪

**CONTENT**

Regulation No. 400/2017
Ethiopia National Anti-Doping Office Establishment Council of Ministers Regulation ………………Page 9592

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻/፪ሺ፱

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባካሄደው አራተኛ ልዩ ስብሰባ ስፖርትን በተመለከተ የወጣውን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ዓለም አቀፍ ስምምነትን በአዋጅ ቁጥር ፭፻፶፬/፲፱፻፺፱ ያፀደቀው በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

Council of Ministers Regulation No. 400/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIA NATIONAL ANTI-DOPING OFFICE

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the International Conventions Against Doping in Sport at its 4th extra ordinary session held on the 7th day of July, 2007; with Proclamation No.554/2007;

**NOW,THERE FORE**, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 39 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 916/2015.

### PART ONE
### GENERAL

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as the "Ethiopia National Anti-Doping Office Establishment Council of Ministers Regulation No. 400/2017".

2. **Definition**

   Without prejudice to the definition provided for in appendix "1" of the World Anti-Doping Code, in this Regulation:

https://chilot.me



## ፪. ትርጓሜ

በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አባሪ ፩ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ

( ፱ሺ፭፻፺፫

፩/ “የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ” ማለት ማንኛውንም በስፖርቱ ውስጥ ያለን አትሌት የሚረዳ ወይም አብሮ የሚሰራ አሰልጣኝ፣ አለማማጅ፣ ማናጀር፣ ወኪል፣ የቡድን ሠራተኞች፣ ኃላፊዎች፣ የህክምና ሠራተኞች፣ ወጌሻዎች፣ ወላጆች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ነው፤

፪/ “ዶፒንግ” ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ በአለም አቀፉ የፀረ-ዶፒንግ ሕግ ከአንቀጽ ፪.፩ እስከ ፪.፲ የተዘረዘሩት የፀረ-ዶፒንግ ሕግ መጣስ ክስተት ነው፤

፫/ “የአበረታች ቅመሞች ቁጥጥር” ማለት ከምርመራ ውጤት ሥርጭት ዕቅድ እስከ ይግባኝ ሰምቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚወሰንበት ያሉትን ሁሉንም ደረጃዎችና ሂደቶች አካቶ የአድራሻ መረጃዎችን መሰብሰብን፣ ለምርመራ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውም ናሙና መውሰድንና ማከማቸትን፣ የላቦራቶሪ ምርመራን፣ በህክምና ምክንያት የሚፈቀዱ መድኃኒቶችን ማጣራትንና መፍቀድን፣ እስከ ውጤት አያያዝ እና መስማት ድረስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት እና ደረጃዎች የሚያጠቃልል ነው፤

፬/ “ፌዴሬሽን” ማለት በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጠውና ከዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የስፖርት አሶሲየሽን፣ የስፖርት ፌዴሬሽን እና የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴን የሚያካትት የስፖርት ማህበር ነው፤

፭/ “ፈቃድ” ማለት ለፕሮፌሽናል የስፖርት አካል፣ ለአሰልጣኝ፣ ለወኪል፣ ወይም ለስፖርት ሙያተኛ አስፈላጊውን የስፖርት ተግባር ለማከናወን እንዲችል ተብሎ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፮/ “ሚኒስቴር” ማለት የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር

1/ “athlete support personnel” means any coach, trainer, manager, agent, team staff, official, medical, paramedical personnel, parent or any other person working with, treating or assisting an athlete participating in or preparing for sports competition;

2/ “doping” means the occurrence of one or more of the anti-doping rule violations set forth in Article 2.1 through Article 2.10 of the World Anti-Doping Code;

3/ “doping control” means all steps and processes from test distribution planning through to ultimate disposition of any appeal including all steps and processes in between such as provision of whereabouts information, sample collection and handling, Laboratory analysis, Therapeutic Use Exemptions (TUEs), results management and hearings;

4/ “federation” means a Sport Association, Sport Federation and Ethiopian Paralympics’ Committee recognized by the Ministry and affiliated to an International Federation;

5/ “license” means a certificate issued to a professional sports body, coach, agent, or a professional sports person for the purposes of carrying out the activities of the relevant sport;

6/ “Ministry” means the Ministry of Youth and Sports;

7/ “National Olympic Committee” means the Ethiopian Olympic Committee, recognized by Ministry and affiliated to the International Olympic Committee;

https://chilot.me



ነው፤

፯/ “ብሔራዊ የኦሎምፒክ ኮሚቴ” ማለት በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጠውና ከዓለም አቀፉ የኦሎምፒክ ኮሚቴ ጋር ግንኙነት ያለው የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ነው፤

፰/ “ጽሕፈት ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ነው፤

፱/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲/ “እውቅና የተሰጠው የስፖርት ድርጅት” ማለት ስፖርትን ለማሳደግ በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ነው፤

፲፩/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ያጠቃልላል፤

፲፪/ “አህጉራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ድርጅት” ማለት በአባል አገራት አማካይነት የተቋቋመ የፀረ-አበረታች ቅመሞች የሕግ ማዕቀፎች የአባል አገራት ሕግ አካል እንዲሆኑ እና እንዲተገበሩ የማድረግ፣ የማቀድና ናሙና የመሰብሰብን፣ የናሙና ውጤት አያያዝን፣ በህክምና ምክንያት የሚፈቀዱ መድኃኒቶች አሰራር ክለሳን፣ የችሎት አሰያየምን እና በአህጉር ደረጃ የትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን ጨምሮ እነሱ በሚወክሏቸው አካባቢዎች ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን የሚመራና የሚያስተባብር ድርጅት ነው፤

፲፫/ “የምዝገባ ምስክር ወረቀት” ማለት አስፈላጊውን የስፖርት እንቅስቃሴ ለመምራትና ለማስተዳደር ለስፖርት አካል የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ነው፤

፲፬/ “የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ስምምነት” ማለት ጥቅምት ፱ ቀን

8/ “Office” means the National Anti-Doping Office of Ethiopia;

9/ “person” means any Natural Person or juridical body;

10/ “recognized sports organization” means a body registered in Ethiopia for the purposes of promoting sports;

11/ “State” means any Regional State referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

12/ “Regional Anti-Doping Organization” means a regional entity designated by member countries to coordinate and manage delegated areas of their national anti-doping programs, which may include the adoption and implementation of anti-doping rules, the planning and collection of samples, the management of results, the review of Therapeutic Use Exemptions (TUEs), the conduct of hearings, and the conduct of educational programs at a regional level;

13/ “registration certificate” means a certificate issued to a sports body for the purposes of carrying out the activities of the relevant sport;

14/ “United Nations Education Scientific Cultural Organization (UNESCO) Convention” means the International Convention against Doping in Sport adopted by the 33rd session of the UNESCO General Conference on 19 October 2005, including any and all amendments adopted by the States Parties to the Convention and the Conference of Parties to the International Convention against Doping in Sport;

https://chilot.me



፲፱፻፺፰ ዓ.ም በተደረገው ፴፫ኛው የድርጅቱ ስብሰባ ላይ የፀደቀው የፀረ-አበረታች ቅመሞች ስምምነት ሲሆን፣ የስምምነቱ ፈራሚ አገራት በስፖርት ላይ የፀረ-አበረታች ቅመሞች አቋምን በመውሰድ በስምምነታቸው ላይ ያደረጓቸውን ማናቸውንም ማሻሻያዎች የሚያጠቃልል ነው፤



፲፭/“የዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ” ማለት በዓለም ዙሪያ ከዶፒንግ ነጻ የሆነ የስፖርት እንቅስቃሴን ለማስተባበር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

፲፮/“የዓለም አቀፍ የፀረ- አበረታች ቅመሞች ሕግ” ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን የስፖርት ፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴን ለማቀናጀት በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ የተዘጋጀ ሕግ ነው፤

፲፯/በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት
## ስለመቋቋም

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ “ጽሕፈት ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ሆኖ የፋይናንስ፣ አስተዳደራዊ እና ሌሎች የየዕለት ተግባራትን ራሱን ችሎ ያከናውናል፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ከማንኛውም መንግስታዊ አካል እና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ጣልቃ

15/“World Anti-Doping Agency (WADA)” means a World Anti-Doping Agency established to lead a collaborative movement for doping-free sport;

16/“World Anti-Doping Code (WADC)” means the Code developed by the World Anti-Doping Agency as a regulation for the purposes of unifying anti-doping activities globally;

17/any expression in the masculine gender shall include the feminine;

## PART TWO
## ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIA NATIONAL ANTI-DOPING OFFICE

### 3. Establishment

1/ There is established the Ethiopia National Anti-Doping Office (in this Regulation to be referred as the “Office") as an autonomous Federal Government office having its own legal personality.

2/ The Office shall be accountable to the Ministry and shall perform its financial, administrative and other daily activities independently.

3/ The Office shall execute its powers and duties free from interference of any governmental and nongovernmental organization or individual.

### 4. Head Office

The head office of the Office shall be in Addis Ababa.

### 5. Objectives of the Office

To promote doping free sports nationwide and aspire the successful and healthy athletes to be burgeoned, the Office shall have objectives to:

1/ enhance the awareness of the society about doping through education, training and mass mobilization;

https://chilot.me



ገብነት ነፃ ሆኖ ይሰራል፡፡

፫. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡

፬. <u>ዓላማ</u>

በአገር አቀፍ ደረጃ ዶፒንግን በመከላከልና በመቆጣጠር ንፁህ ስፖርት እንዲስፋፋና ውጤታማ አትሌቶች እንዲፈሩ ለማድረግ ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩል፦

፩/ የተለያዩ የትምህርት፣ የሥልጠና እና የሕዝብ ንቅናቄ ተግባራትን በማከናወን በዶፒንግ ዙሪያ በሕዝቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፤

፱ሺ፭፻፺፮

፪/ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ወይም በሚኖር የውጭ አገር ዜግነት ያለው አትሌት ላይ በየጊዜው የተለያዩ ምርመራዎችን በማካሄድ እና የኢንተለጀንስ ተግባራትን በማከናወን አበረታች ቅመሞችን ተጠቅመው በሚገኙበት ወቅት ክስ በማቅረብ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፫/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፯(፳፯) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ የስፖርት ማህበራትን፣ ክልሎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በመደገፍ የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴን ያስተባብራል፡፡

፭. <u>የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ጽሕፈት ቤቱ በአለም አቀፉ የፀረ- አበረታች ቅመሞች ህግ እና አለም አቀፍ መስፈርት መሰረት በስፖርቱ ውስጥ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ በቀጥታ ተፈፃሚ የሚሆኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕጉን ጨምሮ ከዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ሕጎችና ደንቦች ጋር የተጣጣመ እና በየደረጃው ዶፒንግን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ፖሊሲ እና የማስፈፀሚያ

2/ undertake different doping tests on all athletes who are nationals, residents, license holders or members of sport organizations in Ethiopia or who are present in Ethiopia, intelligence activities and the required prosecutions while the athletes tested positive;

3/ without prejudice to Article 6 (27) of this regulation , coordinate all the national anti-doping activities through providing the intended support for the National Sport Federations, Regional or City Administrations and other stakeholders.

## 5. Powers and Duties of the Office

In accordance with the respective provisions of the Code and the International Standards, the office shall have the following powers and duties that shall be automatically recognized by any person who involves in the sporting activities of Ethiopia፡

1/in order to prevent doping, the Office shall develop and implement national anti-doping policy and strategy that are compliance with the rules and regulations of WADA including WADC;

2/ develop and implement trainings and awareness creation programs for the education of the community in general, and the sporting community in particular, about doping and its dangers in sport;

3/ adopt and implement various guidelines and international standards based on the contexts of the country as adopted and amended from time to time by WADA;

4/ carry out doping tests on athletes;

https://chilot.me



ስትራቴጂ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፪/ በየደረጃው ህብረተሰቡንና በተለይም ደግሞ የስፖርቱን ማህበረሰብ በዶፒንግ እና በስፖርቱ ውስጥ በሚያስከትላቸው ጉዳቶች ዙሪያ ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ የሥልጠናና የግንዛቤ መፍጠሪያ ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ ተግባራዊ ያደረጋል፤

፫/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በየጊዜው ማሻሻያ ተደርጎባቸው የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬/ አትሌቶች ላይ የዶፒንግ ምርመራዎችን ያካሂዳል፤



፭/ የዶፒንግ ሕግን በሚጥሱ አትሌቶች እና የአትሌት ደጋፊ ሠራተኞች ላይ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፪ ፣ ፲ እና ፳፫.፪.፪ መሠረት ቅጣት ይጥላል፤

፮/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እና በየጊዜው በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በሚወጡ እና ማሻሻያ በሚደረግባቸው የተለያዩ መመሪያዎች እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች መሠረት ለአትሌቶች፣ ለአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሁም ለዶፒንግ ቁጥጥር ባለሞያዎች ከናሙና አሰባሰብ ሂደት እና ምርመራ ጋር በተያያዘ ተከታታይ መረጃ ይሰጣል፤

፯/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፲፬.፬ መሠረት የመንግሥትንና የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ግዴታዎችን ለማሟላት ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየዓመቱ መረጃዎችን ይሰጣል፤

፰/ የስፖርተኞች ጤና እና ደህንነት በአግባቡ እንዲጠበቅ ለማድረግ በውድድርና መዝናኛ ስፖርቶች ላይ ከተከለከሉና በሰው ሰራሽ መንገድ

5/ penalize any athlete and athlete support personnel who commit doping crimes provided for under Article 2, 10 and 23.2.2 of the WADC;

6/ provide continuous information to athletes, athlete support personnel and doping control officers on the procedures of collecting of samples and testing in accordance with the WADC and the International Standards developed by WADA as may be amended from time to time;

7/ provide the intended information on the execution of the anti-doping programs yearly for the compliance of governmental and world anti-doping standards as provided for under Article 14.4 of the WADC;

8/ promote participation in competitive and recreational sport free from the use of prohibited substances or methods intended to artificially enhance performance thereby rendering impermissible doping practices which are contrary to the principles of fair play and medical ethics, in the interest of the health and well-being of sport persons;

9/ protect the anti-doping rule violations in accordance with Article 2 of the WADC;

10/ establish the Result Management Committee to oversee the anti-doping rule violations as per the WADC and Ethiopia Anti-Doping Directives;

11/ without prejudice to sub-article (10) of this Article, cause the Result Management Committee to discharge its function as the first instance panel to take disciplinary measures on doping related cases as per the Ethiopian Anti-Doping Directives;

https://chilot.me



የአካል ብቃትን ለማሻሻል ከሚዘጋጁና ከተከለከሉ የዶፒንግ ዘዴዎች የፀዳ ፍትኃዊ የውድድርና ተሳትፎ ሥርዓት እንዲኖር ያበረታታል፤

፱/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፬ መሠረት የአበረታች ቅመሞች የሕግ ጥሰት እንዳይፈፀም ይከላከላል፤

፲/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕጎችና በኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሠረት የአበረታች ቅመሞች የሕግ ጥሰቶች ጉዳይን የሚመለከት የውጤት አስተዳደር ኮሚቴ ያቋቁማል፤

፲፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጤት አስተዳደር ኮሚቴው በኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሰረት ዶፒንግን በሚመለከቱ ጥፋቶች ዙሪያ የዲስፕሊን እርምጃዎችን ለመውሰድ የመጀመሪያ ፱ሺ፭፻፺፰ ኑሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ እንዲሰራ ያደርጋል፤

፲፪/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፬.፬ መሠረት የተደነገገው የሥልጣን ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የተከለከሉ አበረታች ቅመሞች ለህክምና አገልግሎት እንዲውሉ ለማድረግ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ገምግሞ የሚወስን የህክምና ንዑስ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

፲፫/ በስፖርት ውስጥ የሚፈጸሙ ከዶፒንግ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ምርመራ ያደርጋል፤

፲፬/ ከአህጉር እና ከዓለም አቀፍ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤

፲፭/ የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ፣ ሌሎች ስምምነቶች እና የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት የፀረ-አበረታች ቅመሞች ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል፤ የዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ዶፒንግን

12/ without prejudice to the jurisdictional limitations of TUEs provided for under Article 4.4 of the WADC, establish an independent Therapeutic Use Exemption (TUEs) Committee to evaluate all requests for therapeutic use exemptions;

13/ carry out investigations regarding matters of doping in sports;

14/ work in coordination and cooperation with Regional and World Anti-Doping Agencies;

15/ make sure whether World Anti-Doping Agency's Anti-Doping Codes, other conventions and UNESCO'S Anti-Doping Convention are properly followed in the country thereby supporting WADA's efforts to prevent doping substances;

16/ pass partial or comprehensive monetary and other sport affiliated support sanctions provided for athletes, federations and other sport organizations from those individuals and organizations who are convicted of breaking procedures and rules recognized by the World Anti-Doping Code;

17/ follow up public and government monetary, material and human resource support sanctions on athletes and athlete support personnel resulting from doping related punishments as per sub-article (5) of this Article and executes consequences that are explicitly stated in the Article 10 and 23.2.2 of the World Anti-Doping Code;

https://chilot.me



ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፮/ የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ ጥሰው ከተገኙ እና የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈባቸው ማናቸውም ግለሰቦች እና ድርጅቶች በተገኙና ለአትሌቶች፣ ለፌዴሬሽኖች እና ለስፖርት ድርጅቶች በሚሰጡ የተወሰኑ ወይም ሁሉም የገንዘብ እና ከስፖርት ጋር የሚዛመዱ ድጋፎች ላይ እገዳ ይጥላል፤

፲፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ መሠረት የዶፒንግ ጥሰት በመፈጸማቸው ምክንያት በአትሌቶች እና በአትሌት ደጋፊ ሠራተኞች ላይ የተጣለ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል እና ከስፖርት ጋር የሚዛመዱ ቅጣቶች በመንግሥትና በሕዝባዊ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤ በዓለም አቀፍ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፲ እና ፳፫.፪.፪ በግልጽ የተዘረዘሩ ውጤቶችንም ይተገብራል፤



፲፰/ ሁሉም የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ሌሎችም አካላት ዶፒንግን ከአገሪቱ ለማስወገድ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች ለጽሕፈት ቤቱ እንዲሰጡ ያበረታታል፤ ይደግፋል፤

፲፱/ በስፖርት ዶፒንግ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ጥናትና ምርምር እንዲደረግም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፳/ የፀረ-አበረታች ቅመሞች አስተዳደር እና ሥራ አመራር ሥርዓትን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፩/ በፀረ-አበረታች ቅመሞች በሕጉ መሠረት አድራሻ ይመዘግባል፤ የተመዘገበው የምርመራ ማህደርም በፀረ-አበረታች ቅመሞች አስተዳደርና ሥራ አመራር ሥርዓት ውስጥ እንዲያዝ ያደርጋል፤

18/ promote and support all service providing government bodies of Ethiopia and other organs to feed the office with doping related information that helps to eliminate doping substances in Ethiopia;

19/ undertake research, co-ordinate and facilitate conditions necessary for research to be undertaken in the field of doping practices in sport;

20/ implement the Anti-Doping Administration and Management System (ADAMS) program;

21/ maintain whereabouts and hold the registered testing pools through including in the Anti-Doping Administration and Management System (ADAMS) in accordance with the Anti-Doping Code;

22/ protect the privacy of Athletes and other persons subject to the Office's Anti-Doping directives;

23/ automatically adopt and implement the prohibited list of doping substances as published and amended by WADA;

24/ accredits independent participant observers at the national anti-doping activities carried out at different levels nationwide;

25/ select preferred Laboratories for its collected samples analysis among those accredited or approved by WADA during inspection and test periods as per Article 6.1 of the WADC;

26/ summon, investigate and call for any evidence that may be required to investigate doping matters;

https://chilot.me



፳፪/ጽሕፈት ቤቱ ባወጣው የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሠረት የአትሌቶችንና የሌሎች አካላትን የግል መብት ይጠብቃል፤

፳፫/የተከለከሉ አበረታች ቅመሞችን ዝርዝር በተመለከተ በየጊዜው በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ አማካይነት የሚደረገውን ማሻሻያ ወዲያውኑ በመቀበል ተፈፃሚ ያደርጋል፤

፳፬/በአገር አቀፍ ደረጃ በየእርከኑ የሚካሄደውን የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴ ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለሚታዘቡ ታዛቢዎች ተገቢውን እውቅና ይሰጣል፤

፳፭/ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ ፬.፩ መሠረት የናሙና ትንተና ሲካሄድ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እውቅና ከተሰጣቸው የምርመራ ላብራቶሪዎች መካከል ይመርጣል፤

፳፮/ከዶፒንግ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ የሚያስፈልግ ማንኛውም ማስረጃ እንዲቀርብለት መጥሪያ መላክ፣ ምርመራ ማድረግ ወይም ማዘዝ

፱ሺ፮፻ ኣ፤

፳፯/ በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነ ዶፒንግን የመመርመር እና የመቆጣጠር ሥልጣኑን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፰/ ሥራዎችን በተገቢው መንገድ በማከናወን ዓላማውን ለማስፈፀም ውል ይዋዋላል፤ የንብረት ባለቤትና ባለይዞታ ይሆናል፤ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፱/በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፳፰) የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራትን በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ በልዩ ሁኔታ ለዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች እና ዋና ዋና የስፖርት ኩነት የሚያዘጋጁ አካላት ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ጋር ተጣጥመው እንዲፈፀሙ ያደርጋል፡፡

27/ exercise the exclusive jurisdictions of doping tests and controls in Ethiopia;

28/ enters into contracts for or in connection with the performance of its functions and the attainment of its objects; acquire, hold and dispose of property; sue and be sued in its own name;

29/ implement its exclusive powers and duties set out from sub-article (1) to (28) of this Article in line with the exceptional jurisdictions of International Federations and Major Event Organizations set forth in the World Anti-Doping Code.

**7. Organization of the Office**

The Office shall have:

1/ a Management Board (to be referred as "Board");

2/ a Director General, and as may be necessary, Deputy Director General to be appointed by the Government;

3/The necessary staff.

**8. Members of the Board**

1/ The Board shall have five to seven members, including the Chairperson, to be appointed by the Government.

2/ The Director General of the office shall participate in the meeting as member of Board and Secretary of the meeting.

3/ The following persons shall not be appointed to serve as Chairperson or members of the Board:

a) a supplier or is associated with any person who supplies goods to the Office; or

b) an employee of the office or family member of any one employed in the office; or

c) holds office in a political party; or

d) a member of an elective body; or

https://chilot.me



**፯. <u>የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት</u>**

ጽሕፈት ቤቱ፡-

፩/የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/በመንግስት የሚሰየም ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣

፫/አስፈላጊ ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

**፰. <u>ስለቦርድ አባላት</u>**

፩/ ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከአምስት እስከ ከሰባት የሚሆኑ በመንግስት የሚሰየሙ አባላት ኖሩታል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል እና ጸሐፊ በመሆን በስብሰባው ላይ ይሳተፋል፡፡

፫/ የሚከተሉት ሰዎች የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ሆነው መሰየም አይችሉም፡-

ሀ) ለጽሕፈት ቤቱ የንግድ ዕቃዎችን የሚያቀርብ ሰው ወይም ቅርበት ያለው አካል፤ ወይም

ለ) የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኛ እና የሠራተኛው የቤተሰብ አባል፤ ወይም

ሐ) የፖለቲካ ፓርቲ አመራር፤ ወይም

መ) የማንኛውም ምክር ቤት አባል፤ ወይም

፱ሺ፮፻፩

ሠ) አትሌቶች፣ የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ ፌዴሬሽኖች እና የስፖርት ድርጅቶች፤ ወይም

ረ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) ሥር ከተጠቀሱት ድርጅቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው፤ ወይም

ሰ) በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ወንጀል ፈጽሞ ሥልጣን ባለው በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ያልተሰየመ ሰው፤ ወይም

ሸ) በጤና እክል ወይም በአዕምሮ ሕመም ሳቢያ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የማይችል ሰው፡፡

**፱. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

e) an athlete or an athlete support personnel or sports federations or sport organization; or

f) a person affiliated with the organizations mentioned under paragraph (e) of this Regulation; or

g) any person who has been convicted of criminal offence by a court of law whether in Ethiopia or elsewhere and yet not re-instated; or

h) any person who has a health or mental illness and not capable to perform the functions of the office.

**9. <u>Powers and Duties of the Board</u>**

The Board shall have the following powers and duties:

1/ formulate policies and strategic as well as strategic plan; conduct monitoring and evaluations of same and give direction;

2/ evaluate and forward its recommendations on policies, strategies, plans, studies, and researches formulated with the view to eliminate doping in Sport;

3/ establish relevant committees as it deems convenient for the efficient carrying out of its mandate such as Committee on Result Management, Committee on Therapeutic Use Exemption, Committee on Research and others;

4/ determine the number of members of Committees to be established pursuant to sub-article (3) of this Article;

5/ designate Chairperson of each Committee from the members of the Board ;

6/ co-opt persons having required expertise to assist committees;

7/ advice the Office on its daily activities;

8/ carry on any other activities that enable to achieve the objectives of the Office.

https://chilot.me



ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ በፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች እንዲሁም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም በመከታተልና በመገምገም አቅጣጫ ማስቀመጥ፤

፪/ የስፖርት ዶፒንግን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶች፣ ጥናቶች እና ምርምሮች ዙሪያ ግምገማ በማድረግ የውሳኔ አስተያየት ማቅረብ፤

፫/ እንደ አስፈላጊነቱ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የውጤት አስተዳደር፣ የተከለከሉ ቅመሞችን ለህክምና መጠቀምን የሚመለከት፣ የጥናት እና ምርምር እና ሌሎች ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱትን የእያንዳንዱን ኮሚቴ አባላት ብዛት የመወሰን፤

፭/ ለእያንዳንዱ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚሆነውን የሥራ አመራር ቦርድ አባል የመሰየም፤

፮/ ልዩ ሙያ ያላቸውን ሰዎች በቦርዱ አጋር አባልነት እንዲሳተፉ የመወሰን፤

፯/ ጽሕፈት ቤቱን በዕለት ተዕለት ሥራዎች ዙሪያ ማማከር፤

፰/ ሌሎች የጽሕፈት ቤቱን ዓላማ ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ማከናወን፡፡



## ፲. የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ አስፈላጊ ሲሆን በሰብሳቢው ጥሪ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪/ በስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ ማንኛውም የቦርድ አባል የጥቅም ግጭት ሊያስነሳ

## 10. Meeting of the Board

1/ The Board shall conduct its regular meeting every three months; provided, however, that it may hold extraordinary meetings when called by the Chairperson.

2/ There shall be a quorum where a majority of the members of the Board are present at a meeting.

3/ The decision of the Board shall be passed by a majority vote, in case of a tie; the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Any member of the Board shall be required to declare and cause record his interest in any matter before the Board in which a conflict of interest is likely to arise.

## 11. Term of Office of the Board

1/The term of Office of the Chairperson and Members of the Board shall be four years; provided, how ever, that they may be re-assigned for one additional term of office.

2/ The Government shall substitute the Chairperson or a Board Member, when they leave from board through resignation, health matters or incompetency or other reasons.

3/ When the Chairperson or Members of Board leave from membership due to various reasons as per sub-article (2) of this Article, the Office shall report to the Government for substitution.

4/ The Government shall appoint a substitute Chairperson or Members of Board within three months starting from the report received pursuant to sub-article (3) of this Article.

5/ The term of office of the newly substituted Board Members shall be the remaining term of office of the late Board Member.

https://chilot.me



የሚችል ጉዳይ ሲኖር ለቦርዱ በማሳወቅ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

**፲፩. የቦርዱ የሥራ ዘመን**

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመታት ይሆናል፣ ሆኖም በድጋሚ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

፪/ ከቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አባላት መካከል በራሱ ፍላጎት፣ በህመም፣ በብቃት ማነስ ወይም በመሳሰሉት ምክንያቶች ከቦርድ አባልነት በሚለቅበት ጊዜ ምትክ የቦርድ አባል በመንግሥት ይሰየማል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አባል ከአባልነት በሚሰናበትበት ወቅት በምትኩ እንዲሰየም ጽሕፈት ቤቱ ለመንግሥት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

፬/ መንግሥት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሪፖርት ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ምትክ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ይሰይማል፡፡

፭/ የተተኪ የቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ የለቀቁት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

፱ሺ፮፻፫

**፲፪. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

**12. Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the Chief Executive officer of the office and shall, direct and administer the activities of the office.

2/ Without limiting the generality of Article 13(1) of this Regulation , the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the office specified under Article 6 of this regulation;

b) employ and administer employees of the office in accordance with the Federal Public Service Laws;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work program and budget of the office after review by the Board and implement the same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Office;

e) represent the Office in its dealings with third parties;

f) produce and submit to the Ministry performance and financial report of the Office;

g) perform such other duties as may be assigned to him by the board.

3/ The Director General of the Office may delegate part of his powers and duties to the Deputy Director General and employees of the office to the extent necessary for the effective performance of the activities of the office.

https://chilot.me



ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የጽሕፈት ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ በቦርዱ አስገምግሞ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ይተገብራል፤

መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደ በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት አዘጋጅቶ በቦርዱ አስገምግሞ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሰ) ከቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፱ሺ፮፻፬

**፲፫. የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ዓላማዎች ተግባራዊ በማድረግ፣ ሥልጣንና ተግባራቱን ሥራ ላይ በማዋል፣ የጽሕፈት ቤቱን ተግባራት በማቀድና አስተባብሮ በመምራት ረገድ ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፡፡

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**13. *Power* and Duties of the Deputy Director General**

1/ Assists the Director General in executing the objectives of the agency specified in this Regulation; in implementing Powers and Duties of the office, planning, organizing and coordinating the activities of the office.

2/ carry out such other activities which are may be specifically entrusted to him by the Director General.

3/ Act on behalf of the Director General in his absence.

**14. Budget of the Office**

The budget of the Office shall be allocated by the Government.

**15. Books of Account**

1/ The Office shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The Books of Accounts and financial documents of the Office shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor assigned by him.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**16. Duty to Cooperate**

1/ Any person shall have the duty to co-operate with the office in the implementation of any anti-doping movement and with any investigations conducted by the office.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article:

a) Each Sports Federation shall automatically accept and recognize the anti-doping rules and the Office's results management authority and be bounded by it and produce their own Anti-Doping rules derived from the International Federations and Ethiopian anti-doping rule enforcing all Athletes and each Athlete Support Personnel, Coach, Trainer, Managers, Team

https://chilot.me



፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

**፲፬. <u>በጀት</u>**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

**፲፭.<u>የሒሳብ መዛግብት</u>**

፩/ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዝገብ እና ሰነዶችን ይይዛል፡፡

፪/የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትንና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተሩ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፲፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው በማንኛውም የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴ ውስጥ እና በጽሕፈት ቤቱ በሚከናወን የምርመራ ሥራ ላይ ጽሕፈት ቤቱን የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) እያንዳንዱ የስፖርት ማህበር በፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እንዲሁም በጽሕፈት ቤቱ የውጤት አስተዳደር መመሪያ በቀጥታ ተገዥ ይሆናል፤ በስሩ ባሉ ሁሉም አትሌቶች፣ የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ አሰልጣኞች፣ ማኔጀሮች፣ ወኪሎች፣ የቡድን ሰራተኞች፣ ኃላፊዎች፣ የህክምና ሰራተኞችና ወጌሻዎች እና ሌሎችም ጉዳዩ



ሚመለከታቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ከኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እና ከዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች አሰራር ጋር የተጣጣመ የራሱ የማስፈፀሚያ መመሪያ ያዘጋጃል፤

ለ) የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ ጥሰትን

Staff, officials, medical or Paramedical Personnel;

b) any person shall have duty to report to the Office any information relating to an anti-doping rule violation, and, if it is a National Federation, it shall also report to its International Federation;

**17. <u>Independence</u>**

The Board, Director General, Deputy Director General and staffs of the Office shall discharge their duties free from interference of any person.

**18. <u>Power to Issue Directives</u>**

The Office may develop its own Anti-Doping Directives in accordance with the World anti-doping rules and international standards.

**19. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa this 24th Day of Murch 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me



በሚመለከት ማንኛውም ሰው ለጽሕፈት ቤቱ ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን ብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽን ከሆነ ለዓለም አቀፉ የስፖርት ፌዴሬሽን ጭምር ማሳወቅ አለበት፡፡

**፲፯.የሥራ ነጻነት**

ቦርዱ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እና የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ከማንኛውም ሰው ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው ይሰራሉ፡፡

**፲፰.መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ጽሕፈት ቤቱ የዓለም አቀፍ የፀረ-አበረታች ቅመም ሕጎችን እና ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**